በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን ሚያዚያ 2 8 2012
Date
ቁጥር 4-0/0497/12
Ref.No.

ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u> ፤

ጉዳዩ፡- <u>በመመሪያ ቁጥር 51/2010 አንቀጽ 9(1) የተሰጠ ማብራሪያ መላክን ይመለከታል፡፡</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ሕ/አ/16/32 ሚያዚያ 20 ቀን 2012 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ በመመሪያ ቁጥር 51/2010 አንቀጽ 9(1) የተመለከቱት የግል መገልገያ ዕቃዎች አጠቃለው ወደ አገር እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው ባለመብቶች የመብት አፈፃፀም ላይ በተገልጋዮች በኩል ቅሬታ እየቀረበ መሆኑን ጠቅሰን የመብቱ ተጠቃሚ ወደ "አገር ገባ" የሚባልበት ጊዜ በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጠን የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ.ን በቁጥር 4/0505/12 እንዲሁም ሚያዚያ 07 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር 4/0733/12 በተፃፈ ደብዳቤዎች ለተጠየቁ የማብራሪያ ጥያቄዎች ምላሹን አሳውቋል፡፡

ስለሆነም  የገንዘብ ሚኒስቴር በመመሪያ ቁጥር 51/2010 አንቀጽ 9(1) የተመለከቱት የግል መገልገያ ዕቃዎች አጠቃለው ወደ አገር እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው የመብቱ ተጠቃሚ ወደ "አገር ገባ" የሚባልበት ጊዜ በተመለከተ የላከውን ማብራሪያ 1 ገጽ ለተገቢው አፈፃፀም የላክን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 1
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No. 1

ወንድወሰን ደገፋ ካሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን የጽ/ቤት ኃላፊ

<u>ግልባጭ</u>
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>



☎ +251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር / Ref.No ሓ/ኣ/16/፮፪
ቀን / Date 20 ሚያዚያ 2012

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

በመመሪያ ቁጥር 51/2010 አንቀፅ 9(1) የተመለከቱት የግል መገልገያ ዕቃዎችን አጠቃለው ወደ አገር እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው ባለመብቶች የመብት አፈፃፀም ላይ በተገልጋዮች በኩል ቅሬታ እየቀረበ መሆኑን ጠቅሳችሁ የመብቱ ተጠቃሚ ወደ "አገር ገባ" የሚባልበትን ጊዜ በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጣችሁ የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር 4/0505/12 እንዲሁም ሚያዝያ 07 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር 4/0733/12 በተፃፉ ደብዳቤዎች የጠየቃችሁትን ይመለከታል፡፡

1. ለንግድ የማውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎችን ዝርዝር ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 51/2010 አንቀፅ 9(1) በመመሪያው አንቀፅ 4(2) የተመለከተ ማንኛውም ባለመብት (ተመላሽ ኢትዮጵያዊ፣ ከስደት ተመላሽ፣ አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ በግል ሥራ፣ በቅጥር ወይም በትምህርት ውጭ አገር የቆየ ኢትዮጵያዊ…) የሚያስገባውን የግል መገልገያ ዕቃዎች በሙሉ በአንድ ሰነድ አጠቃሎ ወደ ኢትዮጵያ በገባ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ማስገባት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡

2. አንድ በውጭ አገር ሲኖር የነበረ በመመሪያው ተጠቃሚ የሆነ ባለመብት ወደ ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድ በአካል ሊገባ የሚገባው በኢትዮጵያ ሕጋዊ የየብስ እና የአየር መግቢያ በሮች በኩል ሲሆን፣ ባለመብቱ በሕጋዊ መንገድ የገባ ስለመሆኑ በያዘው የጉዞ ሰነድ ላይ የመግቢያ ፈቃድ ማረጋገጫ የሚሰጠው መሆኑ ይታወቃል፡፡

3. በመሆኑም በመመሪያው አንቀፅ 9(1) የተመለከተ ባለመብት ወደ ኢትዮጵያ ገባ ተብሎ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 የተመለከተው ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው ባለመብቱ በአገሪቱ ሕጋዊ የመግቢያ በሮች ወደ አገር ውስጥ ስለመግባቱ በጉዞ ሰነድ ላይ የተመለከተው የመግቢያ ፈቃድ ማረጋገጫ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

4. በውጭ አገር ባለ የኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት ወይም ሚሲዮን ባለመብቱ ጠቅሎ የሚመለስ ስለመሆኑ ለባለመብቱ የሚሰጠው የድጋፍ ደብዳቤ ባለመብቱ በመመሪያው መሰረት በመብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን በማስረጃነት ሊያቀርብ የሚገባው ሰነድ እንጂ ባለመብቱ ወደ ኢትዮጵያ ስለመግባቱ ማረጋገጫ አይደለም፡፡

5. በመሆኑም ባለመብቱ ወደ አገር ገባ ተብሎ የሚቆጠርበትን ጊዜ ለመወሰን ባለመብቱ ሲኖር ከነበረበት አገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ ቆንስላ ጽ/ቤት ወይም ሚሲዮን ለባለመብቱ የተፃፈለትን ደብዳቤ መሰረት ማድረግ የመመሪያውን ዓላማ የተከተለ አይደለም፡፡

ስለዚህ ባቀረባችሁት ጥያቄ ላይ ያለን ማብራሪያ ከዚህ በላይ የተመለከተው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

letter/was

ስልክ Tel 251-11-155 24 00,22 66 98 / 251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037 — እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia